# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 129 ጥቅምት 25 ቀን 2003 ገጽ 1

### የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

### የወያኔ አገዛዝ ወታደሮች በየረር ገዳም የሚኖሩትን ባህታዊያን ወረሩ፤ የሞቱ የቆሰሉና የታሰሩ ምእመናን እንዳሉ ተዘገበ

በየረር ገዳም የሚኖሩ አንድ ባህታዊ ከሶስት አመት በሁዋላ በኢትዮጵያ አዲስ ንጉስ ይነግሳል ብለው በመተንበያቸው እርሳቸው ያሉበት ገዳም በወታደሮች ተወሯል፤ የሞቱ፣ የቆሰሉና የታሰሩ ምእመናን መኖራቸውን ምንጮች መግለፃቸውን ከኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን - ኢሳት - ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

የኢሳት የአዲስ አበባ ምንጮች እንደተናገሩት "በየረር ዋሻ ውስጥ የሚኖሩት ባህታዊ በሶስት አመት ውስጥ ኢህአዴግን የሚተካ አዲስ ቴዎድሮስ የሚባል ንጉስ ይነግሳል፣ ንጉሱም በዘንግ ብቻ ይገዛል፣ በኢትዮጵያም ጦርነትና ችጋር ይጠፋል፣ ባህታዊውም ከየረር ባታ ይወጣል" ብለው ለጉባኤው ትንቢት ተናግረው ነበር።

ይህን የሰማው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የየረር ተራራን የፌደራል ሰራዊት፣ የፌደራል ፖሊስና የደህንነት አባላትን በመላክ ዙሪያውን ካሳጠረ በሁዋላ፣ ወደ ገዳሙ በማስገባት "ንጉሱን አምጡ" በሚል ባህታዊያንን አስደብድቧል። በድብደባው የሞቱ፣ የቆሰሉና እስካሁን ዱካቸው ያልተገኘ ባህታዊያን መኖራቸውን ኢሳት ምንጮቹን ጠቅሶ ዘግቧል። ጉዳዩን ለማጣራት ወደ ስፍራው ተጉዞ የነበረ አንድ የኢሳት ባልደረባም፣ ድርጊቱ መፈጸሙን እንዳረጋገጠ እና ባህታዊያኑ አሁንም በፍርሀት ውስጥ መሆናቸውን እንደመሰከረ የቴሌቪዥን ድርጅቱ ገልጿል።

ትንቢቱን የተናገሩት ባህታዊ መያዝ አለመያዛቸውን፤ ምን ያክል ባህታዊያን እንደተያዙ፣ ምን ያክል እንደሞቱና ምን ያክል እንደቆሰሉ ለማወቅ እንዳልተቻለም ከኢሳት ያገኘነው ማስረጃ ያስረዳል።

### የአለም ባንክ ውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በየአመቱ ወደ አገራቸው የሚልኩት ገንዘብ መጠን ብሔራዊ ባንክ ከሚለው በሶስት እጥፍ ይበልጣል አለ

የአለም ባንክ በቅርቡ ይፋ ባደረገው የጥናት ውጤት ኢትዮጵያ በየአመቱ ውጭ አገር ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን የምታገኘው ገንዘብ 3.2 ቢሊዮን ዶላር ነው ማለቱን አፍሪክ-ኒውስ የተባለው የዜና አውታር ዘግቧል።

ይህ ቁጥር በወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር ያለው ብሔራዊ ባንክ በየአመቱ ከሚያስቀምጠው በእጥፍ ድርብ የሚበልጥ ነው፤ ብሔራዊ ባንክ በየአመቱ ከስደተኛው ማህበረሰብ የሚገኘውን ገንዘብ ከቢሊዮን ዶላር በታች እንደሚያኖረው ለማወቅ ተችሏል። የአለም ባንክ ጥናት፣ 14 በመቶ የሚሆኑ ለአቅመ አዳም የደረሱ ኢትዮጵያውያን በአመት ቢያንስ 600 ዶላር ከውጭ አገር እንደሚላክላቸውም ገልጿል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

### የታላቁ ሩጫ ቲኬት ገበያ ላይ መሆኑ ሳይታወቅ ተሸጦ ማለቁ አነጋጋሪ ሆኖ ሰነበተ

በ1994 አመት ምህረት በአትሌት ሃይሌ ገብረስላሴ ተቋቁሞ እና በየአመቱ ሲካሄድ የቆየው ታላቁ ሩጫ በዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር ሳይወድቅ እንዳልቀረ የሚያመለክት መረጃ ለግንቦት 7 ድምጽ የዝግጅት ክፍል ደርሷል።

በህዝቡ ዘንድ “የብሶት መግለጫ” የሚል ቅጽል ስም የተሰጠው ዝግጅት፤ በተለይ ከ97ቱ ምርጫ በኋላ ሰላማዊ ሰልፍ እና ስብሰባ የማድረግ ሰብአዊ መብታቸውን በተከለከሉ ወጣቶች የተቃውሞ ድምጽ አሸብርቆ እንደሚያልፍ ይታወቃል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ የላከው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የዝግጅቱ አስተባባሪዎች የዘንድሮው ሩጫ መግቢያ ቲኬት ገና ሳይተዋወቅ ተሸጦ አልቋል ብለው ማወጃቸው (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

### ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የውጭ እርዳታን ለአፈና ማዋሉ መወገዙ እንደቀጠለ ነው

“ሂውማን ራይትስ ዋች” የተባለው አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተሚጋች ድርጅት ሰራተኛ የሆኑት ሚስ ሌስሊ ሌፍኮው ሰሞኑን ባወጧቸው ጽሁፎች የአውሮፓ እና የካናዳ መንግስታት አፋኝ የሆነውን የወያኔ አገዛዝ እየረዱ ነው ብለዋል።

“ሂውማን ራይትስ ዋች” በቅርቡ ባወጣው ሰፊ ሪፖርት፣ ምእራባውያን መንግስታት ለወያኔ በአመት ከ3 ቢሊዮን ዶላር በላይ እየሰጡ እንደሆነና፤ ያም እርዳታ ለዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የጭቆና ስራ እየዋለ እንደሆነ መግለጹን መዘገባችን ይታወሳል።

ሌስሊ ሌፍኮው ዩሮፕ ቮይስ ለተባለው ድረ-ገጽ በጻፉት ጽሁፍ፣ የአውሮፓ አገራት ለወያኔ ከሚሰጠው እርዳታ አንድ ሶስተኛውን እንደሚሸፍኑ እና የአውሮፓ ኮሚሽን ብቻውን በየአመቱ 400 ሚሊዮን ዩሮ ለአገዛዙ እንደሚሰጥ ገልጸዋል። ይህ እርዳታ ደግሞ የድሆችን ህይወት በማሻሻል ስም የሚመጣ ቢሆንም፤ እውነታው ግን ለገዢው ቡድን ድጋፍ ለማሰባሰብ እና የተቃዋሚ አባላት እና ደጋፊዎችን ለመቅጣት ስራ ላይ እየዋለ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ሲቲዚንስ ስፔሻል ለተባለ የካናዳ አገር የመረጃ አውታር በላኩት ጽሁፍ ደግሞ፣ የምእራባውያን መንግስታት ለጋሽ ድርጅቶች አለ የተባለውን ችግር በጽሞና በመመልከት ፈንታ በማስተባበል ላይ የበለጠ ጉልበት ማፍሰሳቸው አስደንጋጭ ነው ብለዋል። የወያኔ አገዛዝ እርዳታን ለፖለቲካ አፈና መጠቀሙ ሰሞኑን እንደገና አለማቀፍ ትኩረት የሳበ ሲሆን፤ የብሪታንያው ቴሌግራፍ ጋዜጣ ሰሞኑን ባወጣው ጽሁፍ የአገሪቱ መንግስት እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አፋኝ መንግስታት የሚሰጠውን እርዳታ እንደገና እንዲያስብበት ጥሪ አቅርቧል።

### የኖርዌይ መንግስት ኦዲተር ጄኔራል የአገሪቱን የእርዳታ ቁጥጥር ሂደት አወገዙ

ኖርዌይ በምግብ ፕሮግራሞች እና በህጻናት እርዳታ ስም የምትለግሰውን ገንዘብ ከሙስና እና ከምዝበራ ለመከላከል የአገሪቱ እርዳታ ሰራተኞች በቂ ስራ እየሰሩ አይደለም ሲሉ የኖርዌይ ኦዲተር ጄኔራል ማውገዛቸው ተዘግቧል።

“ሂውማን ራይትስ ዋች” በቅርቡ ባወጣው ሰፊ ሪፖርት፣ ምእራባውያን በድሆች ስም ለወያኔ አገዛዝ የሚሰጡት እርዳታ ለአፈና ስራ እየዋለ እንዳለ ማጋለጡን መዘገባችን ይታወሳል። ኖርዌይ ከነዚህ ለጋሽ አገራት ውስጥ አንዷ ስትሆን፣ ባለፈው አመት ብቻ ከ41 ሚሊዮን ዶላር በላይ ለዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ መስጠቷ ታውቋል።

“ሂውማን ራይትስ ዋች” በሪፖርቱ ኖርዌይ በአሁኑ ሰዓት ለኢትዮጵያ የምታደርገውን የእርዳታ አሰጣጥ አውግዞ፣ ሂደቱን እንድታሻሽል ጥሪ አቅርቧል። ኖርዌይ ለኢትዮጵያ የምትሰጠው ገንዘብ ለተባለለት ተግባር መዋል አለመዋሉን የምትቆጣጠርበት መንገድ እንደሌላት ለማወቅ ተችሏል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

### አንድ የፌዴራል ፖሊስ ባለስልጣን መታሰሩ ተዘገበ

የፌዴራል ፖሊስ አባል እና የቦሌ አለማቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሰርቬላንስ ክፍል ሃላፊ የሆነ ግለሰብ በሙስና ምክንያት መታሰሩን አፍሪክ ኒውስ የተባለው የዜና ድረ-ገጽ ዘግቧል።

ሳጅን ማሞ ሻሎ የተባለው ግለሰብ አንዲትን ሴት በሽብርተኝነት ታስራ እንደምትከሰስ ነግሮ እራሷን ለማዳን ስትል ጉቦ እንድትሰጠው በማስፈራራቱ ምክንያት መታሰሩን በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የጸረ-ሙስና ኮሚሽን እንደገለጸ ዘገባው አስረድቷል።

ሴቲቱ አስር ሺህ ብር እንድትሰጠው ያስማማት ሳጅን ማሞ፣ የተወሰነውን ክፍያ ሲቀበል እጅ ከፍንጅ መያዙንም ኮሚሽኑ ተናግሯል። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ከወያኔ ባለስልጣናት ትእዛዝ ውጪ እንደማይንቀሳቀስ ይታወቃል። የዝግጅት ክፍላችን ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የሳጅን ማሞ ሻሎን ጉዳይ ከገለልተኛ አካል ለማጣራት ያደረገው ሙከራ አልተሳካም።

የወያኔ አገዛዝ ባለፈው አመት ያጸደቀው የጸረ-ሽብርተኝነት ተብዬ ህግ ዜጎችን ለማሰር ማንኛውም የፖሊስ አባል በሽብርተኝነት ቢወቅሳቸው በቂ ነው ይላል።

## ሰማዕታት ለጣሉብን ኃላፊነት ብቁዎች ነንን? እራሳችንን እንጠይቅ!

ጥቅምት 1998 በዘረኝነት የተለከፉ ሰዎች ጭካኔን፣ በየቤታችን በራፎች፤ በገዛ ዓይኖቻችን ያየንበት ወር ነው። ዘረኛ የሆነ ሰው ከራሱ ዘውግ ውጭ ያሉ ሰዎችን እንደ ጥቃቅን ነፍሳት በመቁጠር እየተዝናና እንደሚጨፈልቃቸው ተመልክተናል። ቀድሞ በአውሮፓ በናዚ ጀርመን፣ በቅርቡ በሰርቪያና በኮሶቮ፤ እንዲሁም በአፍሪካ ሩዋንዳ የታየው ዓይነት የዘር ፍጅት እኛም ላይ ደርሶ አየነው።

ለዓመታት በአስመሳይ ፕሮፖጋንዳ ተሸፋፍኖ የቆየው የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ እውነተኛ ባህርይ የዛሬ አምስት ዓመት በጥቅምት ወር አደባባይ ወጣ። ይህ በጥላቻ የታወረ ዘረኛ በጉልበት የያዝኩትን ሥልጣን በምርጫ ካርድ ሊቀሙኝ ቃጥተዋል ባላቸው ሁሉ ላይ፤ በተለይም ደግሞ ከራሱ ዘውግ ውጭ ያሉትን በሙሉ ሊፈጅ ተነሳ። የቻለውን ያህል ገደለ፤ በሺህዎች በሚቆጠሩ ንጹሃን ዜጎች ላይ የአካል ጉዳት አደረሰ፤ ሚሊዮኖችን አዋረደ።

በአዲስ አበባ፣ በአዳማ፣ በባህርዳር፣ በጎንደር፣ በአዋሳ፣ በሃረር፣ በድሬዳዋ እና ሌሎች ከተሞች እንዲሁም ገጠሮች በሚገኙ ሰላማዊ እናቶችና አባቶች፤ ወጣቶችና ህፃናት ላይ ዘመተ። አግዓዚ የተባለው የክፋት ሠራዊት መርሆዎች ጥላቻ፣ ትዕቢት እና ጭካኔ ነበሩ። በዚህም ምክንያት ደብተርና እርሳሶቻቸውን እንደያዙ ከትምህርት ቤት የሚመለሱ እምቦቃቅላ ህፃናትን ሳይቀር በጥይት ግንባርና ደረታቸውን እየመታ ጣለ።

በጥቅምት ወር 1998 አዲስ አበባ ለመስማት የሚዘገንኑ ጭካኔዎችን አስተናገደች። በጥይት ግንባሩን ተመትቶ ወደወደቀው ታናሽ ወንድሙ የሮጠው ህፃን ደረቱን ተመትቶ የታናሹን ጽዋ ተካፈለ። ባሏ በአጋዚዎች ሲወሰድ ያለቀሰች ሚስት በልጆቿ ፊት በጥይት እሩምታ ተገደለች። እናቶችና እህቶች በማልቀሳቸው ብቻ ጥይት ዘነበባቸው። ታንክና ብረት ለበስ መኪናዎች ድንጋይ በሚወረውሩ ወጣቶች ላይ ተሰማሩ። ሆስፒታሎች በአስከሬኖችና ቁስለኞች ተሞሉ። በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ወደ በረሃ ተጋዙ። የትግራዩ ገዥ ጉጅሌ ለዘመናት የቋጠረውን ጥላቻ በጥቅምት ወር በይፋ አሳየ።

የዚህ ሁሉ ጭካኔ ምንጬ ምንድነው? እውን ሰው በሌላ አምሳያው ላይ ይኸን ያህል መጨከን ይችላል?

በጭራሽ!!! ሰው ብቻ ሳይሆን በጣት ከሚቆጠሩት በስተቀር እንስሳም ቢሆን አምሳያውን አይበላም። ጭካኔን ለመፍጠር "ከራሴ ወገን ውጭ ያለው ሰው በሙሉ ሰው አይደለም" ብሎ ማመን ያስፈልጋል። ዘረኝነት እንዲህ ዓይነቱን የታመመ ጭንቅላት ይፈጥራል። ለዘረኛ ሰው "ሌላው ሰው" ሰው አይደለም። ጥራት ያለውን ሰው ለመፍጠር "ሌሎቹ ሰዎች" መወገድ አለባቸው። እንዲያውም "ምርጦች" ብቻ እንዲፋፉ ሌሎችን ማስወገድ ተፈጥሮን መርዳት አድርጎ የሚወስድ ጭንቅላት ይፈጥራል - ዘረኝነት። ለዘረኛ ጭንቅላት ሌሎች ተባዮችና ተውሳኮች ናቸውና እነሱን ማስወገድ ያሸልማል።

በጥቅምት 1998 ያየነው ይህንን ነው። የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ያደረገው ይህንን ነው። በጉጅሌው እሳቤ መሠረት ወጣት ሽብሬ፣ ህፃን ነቢዩ፣ እናቶችና አባቶች ሰዎች አይደሉም። እንዲያውም ሰው መስለው መፈጠራቸው ስህተት ነው። በጉጅሌው እሳቤ መኖራቸው ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም። ስለሆነም ያለምክንያት ተገደሉ። ገዳዮቻቸው በመግደላቸው ተሾሙ፤ ተሸለሙ።

የጥቅምት ሰማዕታትን የምናስባቸው በጥልቅ ሃዘን ብቻ ሳይሆን በቁጭትና እልህም ጭምር ነው። ወገኖቻችን እንደሰው ባለመቆጠራቸው ተገደሉ። አሁንም እንደሰው የማይቆጠሩ በመሆኑ ሙት ዓመታቸውን መዘከር ወንጀል ነው። መቸ ነው ይህ ውርደት የሚያበቃው?

ሰማዕታቱ የህይወት ዋጋ ከፍለው ዘረኝነትን የማስወገድ ሸክም እኛ ላይ ጥለዋል። ይህንን ኃላፊነት ለመሸከም ብቁዎች ነንን? እያንዳንዳችን የገዛ ራሳችንን እንጠይቅ።

**ዘላለማዊ ክብር ለሰማዕቶቻችን !!!**

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

### የአለም ባንክ ውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከደካማ የመረጃ አሰባሰብ መዋቅር በተጨማሪ፣ በአገዛዙ ቁጥጥር ስር ያለው ብሔራዊ ባንክ ቁጥሩን አሳንሶ የሚናገርበት ፖለቲካዊ ምክንያቶች ሊኖሩት ይችላል ያሉን የፖለቲካ ተንታኝ፥ እውነተኛውን ቁጥር መናገሩ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሃይላቸውን እንዲረዱ ያደርጋቸዋል ብለዋል። ስደተኞቹ በአብዛኛው ወያኔን እንደሚቃወሙ እና ለአገዛዙ የእግር እሳት ሆነው እንደቆዩ ይታወቃል።

የፖለቲካ ተንታኙ እንደሚሉት፣ ይህ ትልቅ ቁጥር ያለው ኢትዮጵያዊ በእጁ ያለውን ሃይል ከተረዳ ለወያኔ አደገኛ ሊሆንበት ይችላል። ጉዳዩን ከህዝብ ቁጥር ጋርም አወዳድረውታል። ባለፈው አመት በወጣው የህዝብ ቆጠራ ውጤት፣ አገዛዙ የአማራን እና የአዲስ አበባን ህዝብ ቁጥር አሳንሶ ማቅረቡ ይታወሳል።

### የኖርዌይ መንግስት ኦዲተር ጄኔራል . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የኖርዌይ የአካባቢ ጥበቃና የውጭ እርዳታ ሚኒስቴር ሶልኸም ጉዳዩን ያስተባበሉ ቢሆንም፤ የኦዲተር ጄነራሉን ሂስ ተከትለው ክትትል እንደሚያደርጉና ስህተቶችን ለማስተካከል እንደሚሞክሩ ገልጸዋል።

በተያያዘ ዜና የስዊድን መንግስት ለኢትዮጵያ የሚሰጠውን እርዳታ ሊቀንስ ነው ሲል የኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች መወያያ መድረክ የተባለው ድረ-ገጽ ዘግቧል። ድረ-ገጹ የስዊድን መንግስት በኢትዮጵያ ባለው የፖለቲካ ሁኔታ ለረዥም ጊዜ ደስተኛ እንዳልነበረ ገልጿል። ዘረኛውና አምባገነናዊው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በስዊድን ያለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ እንዲዘጋ ማዘዙ ይታወቃል።

### የታላቁ ሩጫ ቲኬት ገበያ ላይ መሆኑ ሳይታወቅ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በብዙዎች ዘንድ አነጋጋሪ ሆኖ ሰንብቷል። ከዚህ ቀደም ቲኬቱ መሸጥ ሲጀመር በመገናኛ ብዙሃን እና በትምህርት ቤቶች የማስታወቂያ ዘመቻ ይካሄድ እንደነበር ያስታወሰው ዘጋቢያችን፤ በዚህ አመት ምንም ሳይሰማ ተሸጦ አልቋል መባሉን ጠቅሷል።

ሩጫው ከተጀመረበት አመት አንስቶ አምልጦን አያውቅም ያሉና ዘጋቢያችንን ያናገሩ ሰዎች፤ ቲኬት ሊያገኙ እንዳልቻሉ እና ያገኘ ሰውም እንደማያውቁ ተናግረዋል። በርካታ አስተያየት ሰጪዎች፥ የወያኔ አገዛዝ በሩጫው ላይ የሚገለጹትን ተቃውሞዎች ከወዲሁ ለማፈን ሲል ካድሬዎቹ ቲኬቶቹን ለደጋፊዎች እና ለፓርቲ አባላት እንዲያከፋፍሉ በጅምላ ሳይጠቀልለው አልቀረም ሲሉ ግምታቸውን ገልጸዋል።

አትሌት ሃይሌ ገብረስላሴ በቅርቡ በተካሄደው የገዢው ፓርቲ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ ለወያኔ አገዛዝ ድጋፍ የሚሰጥ ንግግር ማድረጉ እና አንድ ሬከርድ ሲሰብር ለብሶት የነበረውን ከነቴራ ለዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ በስጦታ መልክ ማቅረቡ ይታወሳል። በርካታ አስተያየት ሰጪዎች፥ ታዋቂው አትሌት ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ የንግድ እንቅስቃሴ የሚያደርግ በመሆኑ ድጋፍ እንዲሰጥ ጫና ሳይደረግበት አይቀርም ይላሉ።

በህዳር 12 የሚካሄደው ሩጫ ቲኬቶች ከውጭ አገር ለሚመጡ ሯጮች እስካሁን በሽያጭ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ከድርጅቱ ድረ-ገጽ ለመረዳት የቻልን ቢሆንም፤ የአገር ውስጥ ተሳታፊዎችን በሚመለከት የዝግጅት ክፍላችን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ያደረገው ሙከራ ለጊዜው አልተሳካም።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## አቅሙን ያወቀ ማህበረሰብ ፖለቲካዊ ተጽእኖዎችን ለማድረግ ሊንቀሳቀስ ይችላል!!!

*ከዝግጂት ክፍላችን*

የአለም ባንክ በቅርቡ ባደረገው ጥናት፣ ውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው በየአመቱ የሚልኩት ገንዘብ 3.2 ቢሊዮን ዶላር እንደሚደርስ ገልጿል። ይህ ቁጥር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚያወጣው ቁጥር ጋር እጅግ ይራራቃል። ብሔራዊ ባንክ በየአመቱ ከውጭ ኢትዮጵያውያን ተላከ እያለ የሚያወጣው ገንዘብ አንድ ቢሊዮን ዶላር እንኳ ደርሶ አያውቅም።

3.2 ቢሊዮን ዶላር ማለት የአገሪቱ አጠቃላይ ምርት አንድ አስረኛ ነው። ይህ መጠን ከምእራባውያን ከሚሰጠው እርዳታ ጋር ሲደመር፣ ከአገሪቱ የአጠቃላይ ምርት ከሃያ በመቶ በላይ ይሆናል።

በወያኔ ቁጥጥር ስር ያለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይህንን ቁጥር እጅግ አሳንሶ የሚናገርበት ምክንያት አጠያያቂ ነው። ባንኩ ወይ ደካማ የሆነ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ስለሚጠቀም ነው፣ አልያም አንድ የፖለቲካ ተንታኝ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት እውነተኛውን መጠን በሌላ ፖለቲካዊ ምክንያቶች ለመግለጽ አይፈልግም።

በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለረዥም አመታት ለዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የእግር እሾህ ሆነው መቆየታቸው ይታወቃል። ብዙ የተቃዋሚ ቡድኖችም፣ በተለይ ከ97ቱ ምርጫ በኋላ፣ ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ የሚልኩ ሰዎች በባንኮች በኩል በመላክ ለወያኔ የውጭ ምንዛሬ ከማቅረብ፣ ሌላ መንገድ እንዲፈልጉ ሲያበረታቱ ቆይተዋል። የዝግጅት ክፍላችንን ያናገሩት የፖለቲካ ተንታኝ እንደሚሉት፣ ይህንን ያህል ገንዘብ እየላከ ነው ብሎ በውጭ ለሚኖረው ኢትዮጵያዊ መናገር፣ ስደተኛው ማህበረሰብ አቅሙን እንዲያውቅ ያደርገዋል። አቅሙን ያወቀ ማህበረሰብ ደግሞ ፖለቲካዊ ተጽእኖዎችን ለማድረግ ሊንቀሳቀስ ይችላል።

ብሔራዊ ባንክ እውነተኛውን ቁጥር መግለጽ የማይፈልግበት ሌላም ምክንያት ሊኖረው ይችላል። የኢኮኖሚ እድገት ማምጣቱን ለማሳየት ቁጥር ከመፈብረክ ጀምሮ የማይቃጣው ነገር ለሌለው አገዛዝ፣ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የሚልኩት ገንዘብ በአገሪቱ አጠቃላይ ምርት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው ብሎ መናገር አሳፋሪ ነው። እንግዲህ የቁጥር ጫወታ የወያኔን ህልውና ከማስጠበቅ አኳያ ያለውን ከፍተኛ ስራ ላወቅን፣ ይህ ቢሆን አያስገርመንም።

የአለም ባንክ ባካሄደው ጥናት ከደረሰባቸው ግኝቶች ውስጥ ሌላው፣ 14 በመቶ የሚሆኑት ለአቅመ አዳም የደረሱ ኢትዮጵያውያን፥ በአማካይ በአመት 600 ዶላር የሚሆን ገንዘብ ውጭ አገር ከሚገኙ ዘመዶቻቸው ይደርሳቸዋል የሚል ነው። ይህ የሚያሳየን ገንዘቡ የተከማቸው በተወሰነ የማህበረሰቡ ክፍል ዘንድ መሆኑን ነው።

አገሪቱ ውስጥ ያለው ሃብትም እንደዚሁ ነው፣ በጥቂቶች ዘንድ የተከማቸ ነው።

ብዙውን ጊዜ ኢትዮጵያውያን በነፍስ ወከፍ በቀን ይህን እና ያን ያህል ዶላር ገቢ ያገኛሉ የሚሉ ቁጥሮችን እናነባለን። አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን በቀን በአንድ እና በሁለት ዶላር መካከል ገቢ እንዳላቸው የብዙ ተቋማት ግምት ነው። የአገሪቱ አጠቃላይ ምርት በህዝብ ብዛት ሲካፈል የሚገኘው የነፍስ ወከፍ ገቢ ተብዬም በአመት ከሶስት መቶ ዶላር በላይ ነው።

ይህ መጠን በአለም ላይ እጅግ ዝቅተኛ ከሆኑት ተርታ የሚመደብ እና ለአገራችን ድህነትም እንደ ማስረጃ የሚጠቀስ ቢሆንም፣ አብዛኞቻችንም በየቦታው የሚጠቀሱትን እነዚህን ቁጥሮች እንደዋዛ እያነሳን ብንደግምም፣ እውነታው ግን አብዛኞቹ ኢትዮጵያዊ ያን የተባለውን መጠን እንኳ አለማግኘታቸው ነው።

ወያኔ ሰራሹ የዋጋ ንረት ህዝቡን ከጉስቁልና ወደባሰ ሁኔታ የከተተባቸው ያለፉት አምስት አመታት ይቅሩና፣ ከዛ በፊት እንኳ ቆሎ በልተው እና በቡና እና በውሃ አወራርደው የሚውሉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር እጅጉን ትልቅ ነበር። በወር ሰላሳ ብር ደሞዝ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም ብዙ ናቸው።

ከአገሪቱ ህዝብ 85 በመቶ የሚሆነውን የሚሸፍነው እና ከሄክታር ባነሰች መሬት ላይ የሚያርሰው ገበሬ በአመት አንዴ ወደ ገበያ ከሚወስደው እህል በአማካይ ከአምስት ሺህ ብር በላይ ያገኛል ቢባል ዘበት ነው። ቢያገኝ እንኳ ያን ገቢ የሚካፈለው ከቤተሰቡ ጋር ነውና፣ በቀን አንድ ዶላር የነፍስ ወከፍ ገቢ ሳይሆን የቤተሰብ ገቢ ቢሆን ምናልባት የተሻለ ያስኬዳል።

ከቁጥር ጫወታው ባሻገር፣ የአገራችን ህዝብ አሰቃቂ በሆነ ድህነት ውስጥ እንደሚኖር ግልጽ ነው። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩት እና በየአመቱ የእርዳታ ጥገኞች የሆኑት ዜጎች፣ ከረሃብ የተነሳ በየትምህርት ቤቶች እራሳቸውን እየሳቱ የሚወድቁት ህጻናት ተማሪዎች፣ ወደ ዘረፋ የዞሩት ተስፋ የቆረጡ ወጣቶች፣ እና ሌሎች በድህነት አረንቋ የሚማቀቁ ኢትዮጵያውያን ይህንን ይመስክሩ።

እንግዲህ በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በእጃቸው ያለውን መሳሪያ ተገንዝበዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። እነሱ ዘመዶቻቸውን ለመርዳት የሚልኩት ገንዘብ ለወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሬ በመስጠት እያጠናከረው ይገኛል። በመሆኑም፥ በመንግስት እና በሌላም ህጋዊ መስመሮች ገንዘብ በመላክ የዘረኛውን አገዛዝ እጅ ከማጠናከር፣ ሌላ መንገዶችን እንዲፈልጉ ሲያበረታቱ የቆዩ ቡድኖችን ጥሪ ሊቀበሉ ይገባቸዋል። ይህ ለአገራችን እና ለህዝባችን ማድረግ ከሚገባን ሁሉ ታናሹ ነውና።

## በአዲስ አበባ ዘረፋ እየተስፋፋ ነው ተባለ

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ የሄደውን የኑሮ ውድነት እና ድህነት መቋቋም ያቃታቸው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ወደ ወንጀል መሰማራት እንደጀመሩ እና በከተማይቱ ውስጥ ስርቆት እና ዘረፋ እየተስፋፋ መምጣቱን የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው ዘገባ አመልክቷል።

ዘጋቢያችን የላከው መረጃ እንዳመለከተው፥ ምንም እንኳ በጉዳዩ ላይ አሃዛዊ ማስረጃ ማስቀመጥ በአሁኑ ጊዜ ባይቻልም፣ የወንጀሎቹ ሰለባዎች የሚያሰሟቸው ስሞታዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ ሄደዋል። በርካቶች ጌጣ ጌጦቻቸው፣ ተንቀሳቃሽ ስልኮችን እና የመሳሰሉትን እንደሚዘረፉ መረጃው ያመለከተ ሲሆን፣ ችግሩን በቁጥጥር ስር ማዋል ያልቻለው ፖሊስ በተደጋጋሚ የህብረተሰቡን እርዳታ እንደሚጠይቅም ለማወቅ ተችሏል።

## በአዲስ አበባ ከተማ በሞጥ ላይ ያሉ ነፍሰ ጡሮች የሆስፒታል አልጋ ለማግኘት እንደሚንከራተቱ ታወቀ

የመንግስት ሆስፒታሎች በጉቦ እና በዝምድና ካልሆነ በስተቀር አገልግሎት ወደማይሰጡበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል ሲል የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው መረጃ አመልክቷል።

ከጊዜ ወደጊዜ ብቃታቸው እየጎደለ የሄደው የመንግስት ተቋማት፣ እና በተለይም ሆስፒታሎች፣ የአገልግሎት ደረጃቸው እና ሽፋናቸው ዝቅ እያለ መሄዱን በተደጋጋሚ የዜጎችን ስሞታ በመጥቀስ መዘገባችን ይታወሳል።

ዘጋቢያችንን ያናገሩት አንድ ተጠቃሚ እንደሚሉት፥ ምጥ ላይ ያሉ ባለቤታቸውን ይዘው ከሆስፒታል ሆስፒታል አልጋ ፍለጋ ሲንከራተቱ ለመዋል ተገደዋል። በስተመጨረሻ "አልጋ የለም" ካሏቸው ሆስፒታሎች ውስጥ ባንዱ የሚሰራ ዘመዳቸውን አግኝተው በመማጸን ወዲያውኑ ቦታ እንደተሰጣቸው እና ባለቤታቸውም በሰላም ለመገላገል እንደታደሉ ገልጸዋል።

በየሆስፒታሉ አልጋ ፍለጋ ሲንከራተቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ ብዙ ሰዎችን እንዳዩ የሚናገሩት ግለሰብ፤ ወደ ግል ሆስፒታል ሄደው መታከም የማይችሉ ድሆች እና እንደሳቸው ዘመድ የሌላቸው ሰዎች እጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን አሳስቦኛል ብለዋል።

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በአገሪቱ ውስጥ ከሚያካሄዳቸው የሙብት ረገጣዎች የተነሳ በየአመቱ በአስር ሺሆች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን አገራቸውን እየጣሉ የሚሰደዱ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው የአገሪቱ የተማረ የሰው ሃይል ነው። በተጨማሪም፥ አገዛዙ ቁጥራቸው የማይታወቅ መንግስት ሰራተኞችን በፖለቲካ ምክንያት ከስራ እንደሚያባርር እና ብቃት በሌላቸው ካድሬዎች እንደሚተካ ይታወቃል።

## የህዝብ ንብረት ከሆኑት የቀበሌ መናፈሻዎች የሚገኘው ትርፍ የወያኔ ካድሬዎች ሽልማት ነው ተባለ

የዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት እና ካድሬዎች የኢትዮጵያን ህዝብ ከሚበዘብዙባቸው መንገዶች ውስጥ ብዙ የማይወራላቸው የቀበሌ መናፈሻዎች መሆናቸውን የሚጠቁም መረጃ ሰሞኑን ለዝግጅት ክፍላችን ደርሷል።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሁሉም ቀበሌዎች ሊባል በሚችል ሁኔታ በወሳኝ አካባቢዎች የተቋቋሙ የህዝብ መናፈሻ ማእከላት እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህ መናፈሻዎች ለአካባቢው ሰዎች የስራ እድል ከመፍጠራቸው በተጨማሪ፤ በዝቅተኛ ዋጋ የባር፣ የምግብ፣ የካፌ እና የመዝናኛው አገልግሎቶች ለያሉበት ማህበረሰብ ይሰጣሉ።

ከፍተኛ ገቢ እንዳላቸው የሚነገርላቸው እነዚህ የህዝብ ድርጅቶች ግን ግልጽ የሆነ የገንዘብ አያያዝ መዋቅር እንደሌላቸው ለማወቅ ተችሏል። የአዲስ አበባውን የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ያናገሩ የውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደሚሉት፣ ከነዚህ ተቋማት የሚገኘው ገቢ በቀጥታ የዘረኛው አገዛዝ ካድሬዎች ወደሆኑ የቀበሌ ባለስልጣናት ኪስ እየገባ ነው።

መረጃውን በድብቅ ያቀበሉት ዜጎች ጉዳዩን የሚያጋልጡበት መድረክ እንደሌላቸው እና አለ በሚባለው መንገድ ለመሄድ እንደሚፈሩ ተናግረዋል። ይህ አሰራር የወያኔ አገዛዝ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ካድሬዎቹን ከሚሸልምባቸው መንገዶች አንዱ ነው ብለው እንደሚገምቱ የገለጹት ምንጮች፤ የካድሬዎቹን ስርቆት ብናጋልጥ ተቀጪዎቹ ካድሬዎቹ ሳይሆኑ እኛው ራሳችን እንሆናለን በሚል እንሰጋለን ብለዋል።

## የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የህዝብ ንብረት የሆኑ ድርጅቶችን ወደ ወያኔ የንግድ ኩባንያዎች ለማስተላለፍ እየተሰናዳ እንዳለ ታወቀ

በዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር የሚገኘው ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የህዝብ ንብረት የሆኑ የንግድ ድርጅቶችን ወደ ወያኔ ኩባንያዎች ሊያስተላልፍ በስንድት ላይ እንዳለ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ ዘገባ አመልክቷል።

መረጃው እንደሚለው፥ ኤጀንሲው እንደ ኢትዮጵያ ሆቴል፣ አዳማ ራስ ሆቴል፣ ታቦር ሴራሚክ እና የመሳሰሉትን ድርጅቶች ከአገዛዙ ጋር ትስስር ወዳላቸው ወይም ንብረቱ ወደሆኑ ኩባንያዎች ሊያስተላልፍ ነው።

የገዢው ፓርቲ ንብረቶች የሆኑና በቁጥጥሩ ስር የሚገኙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች አንድ ላይ ከ60 በመቶ በላይ የሚሆነውን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንደሚቆጣጠሩ ይታወቃል። ወያኔ እንደ ኢትዮጵያ ቴሌኮሚውኒኬሽን እና አየር መንገድ ያሉ ተቋማትን እስካሁን ያልሸጠበት ምክንያት የራሱ ሰዎች በነዚህ ተቋማት ውስጥ የስራ ልምድ እስኪያገኙ እየጠበቀ እና በመጨረሻም ወደ ራሱ ቁጥጥር ስር ሊያስተላልፋቸው ነው ሲሉ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ።

## ኢትዮጵያውያን የቡና ገበሬዎች የሚገባቸን ዋጋ ከማግኘት ተገድበናል ሲሉ አማረሩ

በተለያዩ ክፍላተ ሃገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የቡና ገበሬዎች ለምርታቸው በቂ ክፍያ እያገኙ እንዳልሆነ በመግለጽ እንደሚያማርሩ የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ለዝግጅት ክፍላችን በላከው መረጃ ገልጿል።

ገበሬዎቹ እንደሚሉት፥ የቡና ዋጋ አገር ውስጥም ሆነ ውጭ አገር ቢጨምርም፤ እነሱ ግን ከጭማሪው እየተጠቀሙ አይደለም። በነሱ እና በገበያው መካከል ላሉ ኩባንያዎች ቡናቸውን በርካሽ ዋጋ እንዲሸጡ እየተገደድን ነው የሚሉት ገበሬዎች፤ የተጠቀሱት ኩባንያዎች ደግሞ በወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር ያሉ ናቸው ይላሉ።

በዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ስር ባለችው ኢትዮጵያ፤ በርካታ የማህበረሰቡ ክፍሎች ስለ ኑሮ ሁኔታቸው ያማርራሉ። በዚህ ሳምንት የወጣው የሌጋተም ኢንስቲቲውት ሪፖርት፥ ሰማንያ በመቶ የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ተስፋ የላቸውም ማለቱን መዘገባችን ይታወሳል።

ለገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች ካልሆነ በስተቀር በአገሪቱ ውስጥ ስብሰባ እና ሰልፍ ማካሄድ የማይፈቀድ በመሆኑም፤ ዜጎች ምሬታቸውን የሚገልጹበት መድረክ የላቸውም። በቂ ካሳ ይሰጠን በሚል ሰላማዊ ሰልፍ የወጡ የአራት ኪሎ አካባቢ ነዋሪዎች በፌዴራል ፖሊስ እና መከላከያ አባላት መበተናቸው እና የተወሰኑ ሰዎችም መታሰራቸው ይታወቃል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org